የኢትዮጵያፌደራላዊዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ

# ፌደራልነጋሪትጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፹
አዲስ አበባ ነሀሴ ፳፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23th Year No.80
ADDIS ABABA 29th August, 2017

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፰/፪ሺ፱ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ……………………………………………ገጽ፱ሺ፰፻፵

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፰/፪ሺ፱

## የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብን ለማሻሻል የወጣ ደንብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፯/፪ሺ አንቀጽ ፲፱ (፩) (ለ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ፬፻፰/፪ሺ፱ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ማሻሻያ**

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፭/፪ሺ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩/ በደንቡ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ውስጥ "ዐቃቢያነ ሕግ" የሚለው ሐረግ ተሰርዟል፡፡

## CONTENTS

Regulation No. 408/2017

Ethiopian Revenues and Customs Authority Employees Administration Council of Ministers (Amendment) Regulations ……………………………………….Page 9840

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO.408/2017

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO AMEND THE ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY EMPLOYEES ADMINISTRATION REGULATIONS

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and 39 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2008 and Article 19(1) (b) of the Ethiopian Revenues and Customs Authority Establishment Proclamation No.587/2008.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Revenues and Customs Authority Employees Administration Council of Ministers (Amendment) Regulation No. 408/2017".

**2. Amendment**

The Ethiopian Revenues and Customs Authority Employees Administration Council of Ministers Regulations No. 155/2008 is hereby amended as follows:

1/ The word "prosecutors" under sub-article (2) of Article 2 of the Regulation is hereby deleted.



www.chilot.me

፪/ የደንቡ አንቀጽ ፵፩ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፵፩ ተተክቷል፤

"**፵፩. በሠራተኛው መታሰር ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ**

በወንጀል ተጠርጥሮ ሥልጣን ባለው አካል የታሰረ ሠራተኛ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ከእስር ተለቆ ወደ ሥራው ካልተመለሰ የሥራ ውሉ ይቋረጣል፡፡"

፫/ የደንቡ አንቀጽ ፵፮ ነባሩ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተጨምሯል፤

"፪/ ይህ ደንብ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተጀምረው ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በዚህ ደንብ መሰረት ውሳኔ የሚያገኙ ይሆናል፡፡"

**፫. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

2/ Article 41 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Article 41:

**"41. Termination of employment contract due to detention of the employee**

The employment contract of an employee who is suspected of committing a crime and detained by an authorized body shall be terminated if the employee is not released from jail and does not resume work within three months."

3/ The existing provision of Article 46 of the Regulation is numbered as sub-article (1) and the following new sub-article (2) is added:

"2/ Cases pending and not decided before the effective date of this Regulation shall be disposed in accordance with this Regulation."

**3. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication on the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 29th day of August, 2017.**

**HAILEMARIAM DESSALEGNE**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL**

**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me

www.chilot.me

www.chilot.me